# በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ጥያቄዎች እና መልሶቻቸው

## I. የሪፖርት አቅራቢ አካላት ምዝገባን በተመለከተ

**ጥያቄ 1.** ሪፖርት አቅራቢ አካላት ለምዝገባ ሲመጡ ሊያሟሏቸው የሚገቡ ሰነዶች ምንድን ናቸው?

### ሀ. ለንግድ ድርጅት ምዝገባ የሚቀርቡ ሰነዶች

1. ላለቀው የበጀት ዓመት ኦዲት የተደረገ/የተዘጋጀ የንግድ ድርጅቱ እና የኦዲት ድርጅቱ ማህተም ያረፈበት የሂሳብ መግለጫ፣
2. የታደሰ የኦዲት ድርጅቱ የሙያ ሰርትፊኬት ቅጂ፣
3. የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ቅጂ፣
4. የንግድ ስራ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ቅጂ፣
5. መተዳደሪያ ደንብ ቅጂ (ህጋዊ ሰውነት ላለው ድርጅት)
6. መመስረቻ ጽሁፍ ቅጂ (ህጋዊ ሰውነት ላለው ድርጅት)
7. የግብር ከፋይ መለያ ምዝገባ ቁጥር፣
8. የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፣
9. ከተራ ቁጥር 2- 5 ከጀርባው የንግድ ድርጅቱን ማህተም ማሳረፍ፣

### ለ. ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች

1. ላለቀው የበጀት ዓመት ኦዲት የተደረገ/የተዘጋጀ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቱ እና የኦዲት ድርጅቱ ማህተም ያረፈበት የሂሳብ መግለጫ፣
2. የታደሰ የኦዲት ድርጅቱ የሙያ ሰርትፊኬት ቅጂ፣
3. የግብር ከፋይ መለያ ምዝገባ ቁጥር፣
4. በኤጀንሲው የተሰጠ የሲቪክ ማህበራት የምዝገባ ሰርተፊኬት ቅጂ፣
5. የድርጅቱ መመስረቻ ጽሁፍ ቅጂ፣ እና
6. የድርጅቱ መተዳደሪያ ደምብ ቅጂ፣

***የሲቪል ማበረሰብ ድርጅቱ በንግድ ስራ ላይ የተሰማራ ከሆነ***

7. የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ቅጂ፣
8. የንግድ ስራ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ቅጂ፣
9. የግብር ከፋይ መለያ ምዝገባ ሰርተፊኬት ቁጥር፣ እና
10. የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፊኬት ቁጥር፣
11. ከተራ ቁጥር 4- 8 ከጀርባው የንግድ ድርጅቱን ማህተም ማሳረፍ፣

### ሐ. የህብረት ሥራ ማህበራት (ዩኒየን)

1. ላለቀው የበጀት ዓመት ኦዲት የተደረገ/የተዘጋጀ የህብረት ስራ ማህበራቱ እና የኦዲት ድርጅቱ ማህተም ያረፈበት የሂሳብ መግለጫ፣
2. የታደሰ የኦዲት ድርጅቱ የሙያ ሰርትፊኬት ቅጂ፣
3. የፌደራል ወይም የክልል የህብረት ስራ ማህበራት ኤጀንሲ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ቅጂ፣

4. የግብር ከፋይ መለያ ምዝገባ ሰርተፍኬት ቁጥር፣
5. የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፍኬት ቁጥር፣
6. የንግድ ስራ ፈቃድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ቅጂ፣
7. የንግድ ስራ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ቅጂ፣
8. የድርጅቱ መመስረቻ ጽሁፍ ቅጂ፣
9. የድርጅቱ መተዳደሪያ ደምብ ቅጂ፣

**ማሳሰቢያ:** *ሀ) ሪፖርት አቅራቢ አካላት ቦርዱ ያዘጋጀውን ቅፅ በጥንቃቄ ሞልተው፣ በድርጅቱ ስራ አስኪያጅ አስፈርመው እና በእያንዳንዱ ገፅ ማህተም አድርገው ለቦርዱ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።*

*ለ) ምዝገባው የሚከናወነው በውክልና ከሆነ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ የተረጋገጠ የውክልና ደብዳቤ እና ከጀርባ የድርጅቱ ማህተም ያረፈበት የተወካዩ የታደሰ መታወቂያ ኮፒ ይቀርባል።*

**ጥያቄ 2. የህዝብ ጥቅም አለበት ተብሎ ከዚህ በፊት የተመዘገበ ድርጅት በአዲሱ የሪፖርት አቅራቢ መስፈርት በድጋሚ ይመዘገባል ወይ?**

**መልስ፡-** የሪፖርት አቅራቢ አካላት መለያው (Classification) ሲቀየር ድርጅቱ ያለበት መደብ ከተቀየረ መመዝገብ ያስፈልጋል። ደረጃዎቹን ያልተገበረ ከሆነ አዲስ በተሻሻለው መስፈርት እንደገና ይመዘገባል። ነገር ግን ድርጅቱ በቀድሞው መሰረት ተመዝግቦ የደረጃዎቹን ትግበራ የጀመረ ወይም በሂደት ላይ ያለ ከሆነ ድጋሚ ምዝገባ ሳያስፈልገው በዚያው መቀጠል ይኖርበታል።

**ጥያቄ 3፡- ለምን እንመዘገባለን ጥቅሙ ምንድን ነው?**

**መልስ፡-** ሪፖርት አቅራቢ ድርጅቶች የሚመዘገቡት በመለያ መስፈርቶቹ መሰረት የሚገባቸውን ዓለም ዓቀፍ የፋይናንስ ደረጃዎችን በመተግበር በሁሉም ዘንድ ግልፅነትንና ተጠያቂነትን ለማስፈን፣ የሪፖርት አቅራቢ አካላትን አውቆ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና አቅም ግንባታ ስራዎችን ለመስራት፣ ለክትትል፣ ድጋፍና አስፈላጊውን የትግበራ ግምገማ ለማከናወን፣ በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ግንባታ ውስጥ ባላቸው ሚና ከድርጅቶች የውድቀት ስጋት ለመከላከልና ፍትሐዊ እድገትን ለማስቀጠል ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ ነው።

**ጥያቄ 4፡- ለምዝገባ ይኸን ሁሉ ሰነድ ለምን እናመጣለን በንግድ ፍቃድ ብቻ አንመዘገብም ወይ?**

**መልስ፡-** ለመጀመሪያ ጊዜ ብቻ የተመዝጋቢው ድርጅት ሙሉና ትክክለኛ መረጃ መያዝ አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

**ጥያቄ 5፡- የድርጅት ምዝገባ በገቢዎች ቅርንጫፍ መ/ቤት ለምን አይደረግም?**

**መልስ፡-** የድርጅት ምዝገባው በቅርብ ጊዜ በኦንላይን (ዲጂታል) እንዲከናወን እና ደምበኞች ሳይጉላሉ ባሉበት ሆነው የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ቦርዱ እየሰራ ስለሆነ እስከዚያው ምዝገባው በቦርዱ በአካል በመገኘት ይከናወናል።

**ጥያቄ 6፡- የምዝገባ ካርዱ ስለጠፋብን እንዴት ነው መስተናገድ የምንችለው?**

**መልስ፡-** በቀጣይ ምዝገባው በዲጂታል(Online) የሚከናወን ስለሚሆንና በቀላሉ ማግኘት ስለሚቻል በደንቡ መሰረት አስፈላጊውን ክፍያ ፈጽመው ከፋይላቸው በማውጣት ይስተናገዳሉ፡፡

## 2) የሪፖርት አቅራቢ ድርጅቶች የደረጃዎቹ ትግበራ ልየታን (classification) በተመለከተ

**ጥያቄ 1. ሪፖርት አቅራቢ አካላት የተለዩበት መስፈርት/Classification/ ምንድን ነው?**

**መልስ፡-**

ሀ. የሚያወጡትን የግዴታ የምስክር ወረቀት/debt or equity/ ቊጥጥር በሚደረግበት ሥርዓት ዉስጥ ለግብይት ያዋለ/ለማዋል በዝግጅት ላይ ያለ ማንኛዉም ኩባንያ፣

ለ. ባንኮች፣ኢንሹራንሶች እና ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት፣

ሐ. በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉ የልማት ድርጅቶች፣

መ. የአክሲዮን ኩባንያዎች፣

ሠ. በሚመለከተዉ የመንግስት አካል ቁጥጥር የሚደረግበት የጡረታ፣ የፕሮቪደንት ፈንድ እና ተመሳሳይ ተቋም፣

ረ. የህብረት ሥራ ዩኒየኖች፣

ሰ. ቁጥጥር የሚደረግባቸዉ የሽማቾች ማህበራት፣

ሸ. በሚመለከተዉ አካል ቁጥጥር የሚደረግባቸዉ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት፣ እና

ቀ. የኢትዮጵያ የምርት ገበያ አባላት **ሙሉ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን**/full IFRS/**ን ይተገብራሉ።**

### 1. የመጠን መለያ መስፈርቶች

**1.1 ሌሎች የህዝብ ጥቅም ያለባቸዉ ድርጅቶች**

1.1.1 ዓመታዊ ሽያጭ፡- 300 ሚሊዮን ብር እና ከዚያ በላይ፣

1.1.2 ጠቅላላ ሀብት/ንብረት፡- 200 ሚሊዮን ብር እና ከዚያ በላይ፣

1.1.3 ጠቅላላ ዕዳ፡- ከ200 ሚሊዮን ብር እና ከዚያ በላይ፣ እና

1.1.4 የሠራተኛ ቊጥር፡- 200 እና ከዚያ በላይ ያላቸው እና **ከአራቱ መስፈርቶች ቢያንስ ሁለቱን የሚያሟሉ ሙሉ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን**/full IFRS/**ን ይተገብራሉ።**

**1.2 አነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች**

1.2.1 ዓመታዊ ገቢ/ሽያጭ፡ ከ20 ሚሊዮን ብር እስከ 300 ሚሊዮን ብር፣

1.2.2 ጠቅላላ ሀብት/ንብረት፡- ከ20 ሚሊዮን ብር እስከ 200 ሚሊዮን ብር፣

1.2.3 ጠቅላላ ዕዳ፡- ከ20 ሚሊዮን ብር እስከ 200 ሚሊዮን ብር እና

1.2.4 የሠራተኛ ቁጥር ከ20 እስከ 200 ሠራተኛ ያላቸው ሆኖ

**ከአራቱ ቢያንስ ሁለቱን መስፈርቶች የሚያሟሉ ለአነስተኛ እና መካከለኛ ድርጀቶች የሚያገለግለዉን** /IFRS for SMEs/**ን ይከተላሉ።**

## በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ጥያቄዎች እና መልሶቻቸው

በተራ ቁጥር 1.2 የተጠቀሱት አነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች፣ ማንኛውም ኩባንያ በተ.ቁ 2 ላይ ለሌሎች የህዝብ ጥቅም ያለባቸዉ ድርጅቶች የተቀመጡ የመጠን መለያዎችን የማያሟላ ሆኖ፡

ሀ. እዳዉን/የአክሲዮን ድርሻዉን ቁጥጥር በሚደረግበት የካፒታል ገበያ ላይ ያላዋለ/ለማዋል በዝግጅት ላይ ያልሆነ፣

ለ. የብዙ ሰዎችን ሀብት/ንብረት/ የማስተዳደር ኃላፊነት የሌለበት ከሆነ /IFRS for SMEs/ን ይተገበራል፡፡

### ሐ. የጊዜ ማራዘምን (Time Revision) በተመለከተ

**ጥያቄ 1፡- የተሻሻለው የሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜው መቼ ነው?**

**መልስ፡-** **ሀ)** በFull IFRS ለሚያዘጋጁ እስከ 2015ዓ.ም.

**ለ)** በIFRS for SMEs ለሚያዘጋጁ እስከ 2016ዓ.ም. እና

**ሐ)** IPSASs ለሚተገብሩ እስከ 2016ዓ.ም. የጊዜ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

**ጥያቄ 2፡- በመጀመሪያ የጊዜ ሰሌዳ ደረጃዎቹን የተገበርን ምንድን ነው የምናደርገው?**

**መልስ**፡- ደረጃዎቹን ተግባራዊ ያደረጉ እና በሂደት ላይ ያሉ ወደኋላ መመለስ በቀጣይ ትግበራ ድርጅቶችን ለአላስፈላጊ ወጪ የሚዳርግ በመሆኑ ድርጅቶቹ በጀመሩት መቀጠል አለባቸው፤ ያልጀመሩ በአዲሱ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ይተገበራሉ፡፡

### መ. የሂሳብና ኦዲት ሙያ አገልግሎትን በተመለከተ

**ጥያቄ 1. የሂሳብና ኦዲት ሙያ አገልግሎት ባለሙያዎችን መረጃ ከየት ማግኘት እንችላለን?**

**መልስ፡-** ከቦርዱ ዌብሳይት www.aabe.gov.et ላይ Registered የሚለውን በመክፈት የተፈቀደላቸው የሂሳብ እና ኦዲት ድርጅቶች ሙሉ መረጃ ማግኘት ይቻላል፡፡

**ጥያቄ 2. በአለም አቀፍ የሂሳብ ደረጃዎች ትግበራ ላይ ቦርዱ ያግዛናል ወይ?**

**መልስ፡-** ቦርዱ በየጊዜው የሚወጡትን ደረጃዎች በመከታተል ደንበኞች እንዲያውቁት ያደርጋል፣ መተግበሩን ይከታተላል፤ በየደረጃውም ከዋና ዋና ባለድርሻ አካላት ጋር በፈጠረው ጠንካራ ግንኙነት በኩል አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያደርግ ሲሆን ለጥያቄዎችም ምላሽ ይሰጣል፡፡

### ሠ. ሌሎች ጥያቄዎች

**ጥያቄ 1. ደረጃዎቹን ባንተገብር ጉዳቱ ምንድነው?**

**መልስ**፡- በአዋጅ 847/2006 ክፍል 2 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 2(መ) መሰረት ቦርዱ ባወጣው መስፈርት የሚያሟሉ ድርጅቶች መመዝገብና አለም አቀፍ የሂሳብ ደረጃዎችን መተግበር ግዴታና ተጠያቂነትም አለው፡፡

**ጥያቄ 2. በሂሳብ አገልግሎት (Accountancy service) ምን ምን ስራዎች ይሰራሉ?**

**መልስ፡-** የሪፖርት አቅራቢ ድርጅቶችን ወርሃዊና አመታዊ የሂሳብ መግለጫዎች የማዘጋጀትና ለገቢዎች ባለስልጣን የማሳወቅ፣ በታክስ አሰራር ዙሪያ የማማከር፣አለም አቀፍ የሂሳብ ደረጃዎች ትግበራ፣ የኮንቨርሽን አገልግሎት፣ ኦዲትና ተዛማጅ ስራዎች አገልግሎት ያሰጣሉ፡፡

**ጥያቄ 3. የሂሳብ አገልግሎት (Accountancy service)ን የሚሰራው ማን ነው?**

**መልስ፡-** የሂሳብ አገልግሎት (Accountancy service)ን መስጠት የሚችሉት በኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ የሂሳብ ስራ ለመስራት የሚያስችል የሙያ ብቃትና የድርጅት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጣቸውና በየዓመቱ ፈቃዳቸውን በቦርዱ ያሳደሱ ግለሰቦችና ድርጅቶች ናቸው፡፡

**ጥያቄ 4፡- IFRS ከ GAAP ምን የተለየና የተሻለ ነገር አለው?**

**መልስ፡-** አለም አቀፍ የሂሳብ ደረጃዎች (IFRS, IFRS for SMEs & IPSAS) ከGAAP በተሻለ መልኩ ግልጽነትን (transparency)፣ ተጠያቂነትን (accountability) እና ውጤታማነትን ያሳያሉ፤ ወጥነት ያለው፣ ግልፅ እና ማንም በቀላሉ ሊረዳው በሚችል መልኩ የሚዘጋጅ አለም አቀፍ ደረጃ በመሆኑ በእውቀት ላይ የተመሰረተ የኢንቨስትመንት ውሳኔ ለመወሰን ያስችላሉ፤ ደረጃዎቹ መርህን የተከተሉ (Principle based) በመሆኑ ለተጠቃሚው ማንኛውም ማህበረሰብ እና ለአመራሩ በርካታ መረጃዎችን ይሰጣሉ፡፡ በተጨማሪም GAAP አለም አቀፍ ደረጃ ሳይሆን ሀገራት በራሳቸው የህግ እና የእድገት ሁኔታ መሰረት የሚጠቀሙትና ከሀገር ሀገር አዘገጃጀትና አቀራረቡ የተለያየ እና ወጥነት የሌለው፤ ከዚህ አንፃር ኢትዮጵያ የራሷ GAAP የሌላትና በተቋማት የሚዘጋጁ የፋይናንስ ሪፖርቶችም ግልፅነት የጎደላቸው ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በዓለማችን ከ160 በላይ ሀገራት ወደ እነዚህ ደረጃዎች ሙሉ በሙሉ በመግባት ላይ ይገኛሉ፤ አብዛኞቹ ከዓመታት በፊት ተግብረዋል፡፡

**ጥያቄ 5፡- Plc ሆነን ምንም ዓይነት ዓመታዊ ገቢ ሳይኖረን ለወጭ ለምን እንዳረጋለን?**

**መልስ፡-** ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያዎች (Plc) አለም አቀፍ የሂሳብ ደረጃ እንዲተገብሩ የሚገደዱት በዓመታዊ ገቢያቸው ብቻ አይደለም፤ በባህርያቸው (Plc) መሆናቸው በኩባንያው ስም ሊበደሩ ስለሚያስችል፣ ሲደራጁ በርካታ(ከ2 እስከ 50) የአክሲዮን ባለቤቶች ሊኖራቸው ስለሚችል፣ ከፍተኛ ገንዘብ ሊያንቀሳቅሱ ስለሚችሉ፣ በስራቸው በርካታ ሰዎችን ቀጥረው ሊያሰሩ ስለሚችሉና ቢከስሩ በስራቸው ያሉት ሰራተኞችም ሆኑ ባለአክሲዮኖች (ከኩባንያዎቹ ላይ ጥቅም ያላቸው አካላት) ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ የህዝብ ጥቅም እንዳለባቸው የሚታመን በመሆኑ አለም ዓቀፍ የሂሳብ ደረጃውን (IFRS/IFRS for SMEs) መተግበር ግልጽ የሆነ የሂሳብ አሰራር እንዲኖራቸው ስለሚያስችል ነው፡፡

**ጥያቄ 6፡- የሀብት/ንብረት ትመና (Asset Valuation) ግዴታ ነው ወይ?**

**መልስ፡-** የግዴታ አይደለም፡፡ ነገር ግን የሂሳብ ደረጃዎች አውጭው ቦርድ (IASB) የሚያስቀምጣቸው አማራጮችን ባለሙያ በማማከር መጠቀም ይገባል፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ፡-**


በስልክ ቁጥር +251 111540900 ወይም +251 913770550 ይደውሉ፣

Fb:- accounting and auditing board of Ethiopia, AABE/facebook.com

www.aabe.gov.com

AABE